በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ETHIOPIAN CUSTOMS AUTHORITHY

የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE

# የውስጥ ማስታወሻ /INTER OFFICE MEMO/

ቁጥር: ስ/አ/ጽ/ቤት 160/08
ቀን: 22/08/08 ዓ.ም

ለ: ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት
መጋዘን አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ሂደት
ለሕግ ማስከበር የሥራ ሂደት

ከ: ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ/አ/ቃ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት፣

የጥናትና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በደብዳቤ ቁጥር 3.1.0/732/08 በቀን 19/08/2008 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚካሎች፣ መድሃኒቶች፣ የመዋቢያ እቃዎች እና የምግብ ዓይነቶች ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ማረጋገጫ እንዲቀርብ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ አያሳሰብኩ፤ የደብዳቤው ቅጂ ከዚህ ጋር ደብዳቤ የተላከ መሆኑን አገልፃለሁ::

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ:-

- ም/ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት /የጉምሩክ ጉዳዮች/
- ም/ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት /ሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ዘርፍ/

አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በመሆኑም የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ቁጥጥር የሚያደርጉ አካላት የውይይት መድረክ በመ/ቤታችን በኩል ተዘጋጅቶ ምን አይነት እቃን የትኛው የመንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደሚቆጣጠሩ በግልፅ ተለይቶ እስከሚቀርብና የቁጥጥሩ ስርዓት በታሪፍ ቁጥራቸው ተለይቶ በአሲኩዳ++ ሲስተም ውስጥ እስከሚገባ ድረስ የጤና እና ሌሎች ተዛመጅ ጉዳዮች ጊዜ የሚይስጣቸው በመሆኑ የጉምሩክ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት በሚዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሰረት ቁጥጥር እንድታደርጉ እያሳሰብኩ ከኢትዮጵያ የምግብ የመድሀኒትና ጤና እንክብካቤ ቁጥጥር ባለስልጣን የተላለፈውን ደብዳቤ ሁለት ገጽ ኮፒ አባሪ አድርገን የላክንላችሁ መሆኑን እየገለጽን የጉምሩክ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬትም አስፈላጊውን የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ ተደርጎለታል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ፊ.ቃዲ. በ...
የዕጋና ታሪፍ ምደባ አሠራር ፕሮግራም
ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ሥነ ስርዓት አ/ግ/ል/ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት አ/ግ/ል ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባ አ/ግ/ል/ቡድን

<u>ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

ነገር ግን እነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ኬሚካሎች ውጭ ያሉ የቆዳ ፋብሪካዎች፣ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎችና ሌሎች ከጤና ጋር ግንኙነት የሌላቸው ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችና ተቋማት በሚያስመጡዋቸው ኬሚካሎች ላይ ቁጥጥር የማናደርግ መሆኑና እየገለፅን ስበለጠ መረጃም በንግድ ሚኒስቴር በወጣው የንግድ መደብ በንግድ ዘርፍ ቁጥር 65544 እና 65449 ላይ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ከማዳበሪያ በስተቀር እና ሌላ ቦታ ያልተጠቀሱ ኬሚካሎችና የኬሚካል ውጤቶች ላይ ቁጥጥር የሚያደርገው የንግድ ሚኒስቴር እንደሆነ የሚገልፅ ስለሆነ ከዚህ በኋላ ከላይ በስም ከተጠቀሱት ኬሚካሎች ውጭ በማንኛውም ከጤና ጋር ግንኙነት የሌላቸው ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በሚያመጧቸው ኬሚካሎች ላይ ቁጥጥር የማናደርግ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሄራን ገርባ
የኢንስፔክሽንና [illegible]
ምክትል ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፣/

- ለንግድ ሚኒስቴር
- ለኢንደስትሪ ሚኒስቴር
- ለኬሚካል ኮርፖሬሽን
- ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
- ለጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

  አዲስ አበባ
- ለዋና ዳይሬክተር
- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለቅ/ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቅ/ጽ/ቤት

  ኢምመጪአቂባ